የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት
Road Safety & Insurance Fund Service

# የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂዎች የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት አፈፃፀም ረቂቅ መመሪያ

ጥቅምት 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 በተሰጠው ስልጣን እና በአንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት በተሽከርካሪ አደጋ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ ለማድረግና የህክምና ተቋማት ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በወቅቱ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ በማሰብ በ2006 ዓ.ም የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1/2006 የወጣ ቢሆንም በየደረጃው ያሉ የፌደራል እና የክልል ባለድርሻ አካላት በዚህ መመሪያ መሰረት የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂዎች የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት አሰጣጥን ዘመናዊ፤ ቀልጣፋ እና ተደራሽ በማድረግ ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ ለማስቻል ፤ የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂዎች የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ክፍተቶች፤ ተግዳሮቶችን በመቅረፍ የክትትል፤ የቁጥጥር እና የድጋፍ አሰጣጥን በማሻሻል ዜጎችን ተጠቃሚ በማድረግ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶችን ለመቀነስ ፤ በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ጉዳት ለደረሰበት ማንኛውም ሰው ጥቅም ላይ ሲውል የነበረው አስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የገንዘብ መጠን በሚኒስትሮች ምክር ቤት የአረቦ ተመን እና የካሳ መጠን ክፍያ ደንብ ቁጥር 554/2016 መሠረት ማስተካከያ የተደረገበት በመሆኑ አዋጁንና ደንቡን ለማስፈጸም ይህንን መመሪያ አሻሽሎ አውጥቷል።

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት አፈፃፀም መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በፌዴራል መንግስት "የተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 የተሰጠው ትርጉም እንደተተበቀ ሆኖ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1) **"ቢሮ"** ማለት የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ነው፡፡
   2) "**ሚኒስቴር**" ማለት የጤና ሚኒስቴር ነው፡፡
   3) "**አገልግሎት**" ማለት የመንገድ ደህንነት እና የመድን ፈንድ አገልግሎት ነው፡፡
   4) **"ጤና ተቋም"** ማለት ማንኛውም ከኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሃት፣ የጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ወይም ከክልልና ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ህጋዊ ፈቃድ በማግኘት የህክምና አገልግሎት የሚሰጥ የግል፣ ወይም የመንግስት የህክምና ተቋም ነው፡፡
   5) **"አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 16 መሠረት በመንገድ ላይ በደረሰ የተሽከርካሪ አደጋ የተጎዳ ግለሰብ ከአደጋው ቦታ ወደ ህክምና ተቋም በሚጓጓዝበት ወቅት እና በህክምና ተቋሙ ድንገተኛ ክፍል ውስጥ የሚሰጥ የሕክምና አገልግሎት ነው፡፡
   6) **"ተሽከርካሪ"** ማለት ከአካል ጉዳተኛ ተሽከርካሪ ሠረገላና ከብስክሌት በስተቀር በመንገድ ላይ በመንኮራኩር የሚሄድ ማንኛውም አይነት የባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ግማሽ ተሳቢ ወይም ተሳቢ ነው፡፡
   7) **"አዋጅ"** ማለት የተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድህን አዋጅ ቁጥር 799/2005 ነው፡፡
   8) **"የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ፈንድ ወይም የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ገንዘብ"** ማለት የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት አፈፃፀምን በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ በዚህ መመሪያ መሰረት ከመድን ሰጪ ኩባንያዎችና ከአገልግሎቱ በሚገኝ መዋጮ የተቋቋመና በየግዜው የሚተካ ወይም የሚወራረድ የገንዘብ ምንጭ ነው፡፡

9) “**ተጎጂ**” ማለት በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ ማንኛውም ክፍል ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴ ላይ ጉዳት የደረሰበት ወይም ስነ-ልቦናዊ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው ነው፡፡

10)“**ነጻ የአስቸካይ ህክምና አገልግሎት**” ማለት በመንገድ ላይ በደረሰ የተሽከርካሪ አደጋ የተጎዳ ለማንኛውም ሰው በነጻ የሚሰጥ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ነው፡፡

11)"Emergency Ward (ED)” ማለት በህክምና ተቋም የድንገተኛ ክፍል ውስጥ በባለሙያ የሚሰጥ የነፍስ አድን የህክምና አገልግሎት ነው፤

12)"The triage area"፣ ማለት የመጀመሪያ ደረጃ ምርመራ በህክምና ባለሙያ የሚደረግበት ቦታ ነው፡፡

13) "The resuscitation area" ማለት የተለያዩ የነፍስ አድን ሥራዎች የሚካሄዱበት ታ ነው፡፡

14)."The major or general medical area" ማለት በድንገተኛ ክፍል በሚገኝ ተሽከርካሪ ጎማ ያለው አልጋ (Gurney) ወይንም ተጎታች ጋሪ (Trolley) ተጎጂው የሚያርፍበት ቦታ ፡፡

15) “**ቦርድ**” ማለት የመንገድ ደህንነት እና መድን ፈንድ አገልግሎት ቦርድ ነው፡፡

16) “**ፆታ አገላለፅ**” በወንድ ፆታ የተገለፁት በሙሉ ለሴት ፆታ ያገለግላሉ፡፡

3. **የመመሪያው ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዓላማ፡-

1.በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው በህክምና ተቋማት ነጻ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ማግኘቱን ለማረጋገጥ፣

2. የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎቱን የሰጠው የህክምና ተቋም ተገቢውን የክፍያ አገልግሎት በተገቢው ወቅት እንዲያገኝ ለማድረግና

3. የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት በማሳወቅ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተፈፃሚነት ያለው ግልጽ የሆነ አንድ ወጥ አሠራር ለማስቀመጥ ነው፡፡

4. .**የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ጉዳት ለደረሰበት ማንኛውም ሰው የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት በሚሰጥ በማንኛውም የህክምና ተቋም፣ በፖሊስ፣ በትራፊክ ፖሊስ፣ በመድን ሰጪ ኩባንያ፣ በመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት፣በጤና ሚኒስቴር፣ በጤና ቢሮዎች፣ በተሽከርካሪ ባለንብረቶች፣ በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ተጎጂዎች ወይም

በዚህ መመሪያ መሰረት የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት እና ክፍያ የመጠየቅ መብት ባለው ማንኛውም አካል ወይም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ክፍያ አፈፃፀም

5. **የተሽከርካሪ አደጋን ለመድን ሰጪ ስለማሳወቅ**
   1. በአዋጁ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመ በስተቀር መድን ገቢው መድን የተገባለት ተሽከርካሪ አደጋ ማድረሱን ወዲያውኑ ወይም ቢዘገይ በ10 ቀን ውስጥ ለመድን ሰጪው ማሳወቅ አለበት፡፡
   2. በዚህ መመሪያ ንዕስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት መድን ገቢው የደረሰውን አደጋ ከላይ በተጠቀሰው ግዜ ውስጥ ባያሳውቅም ተጎጂው ካሳ የማግኘት መብቱን አያጣም፡፡
   3. የአደጋ ማሳወቂያው መንገድ በእያንዳንዱ የመድን ሰጪ ኩባንያ ጥቅም ላይ እንዲውል በተፈቀደ ማንኛውም ዘዴ ወይም የአደጋ ማሳወቂያ ቅጽ በመሙላት ለሚመለከተው የመድን ሰጪ ኩባንያ በተመዘገበ አድራሻ በማቅረብ ሊሆን ይችላል፡፡

6. **መድን ሽፋን በሌላቸው ወይም ባልታወቁ ተሽከርካሪዎች አደጋን ለአገልግሎቱ ስለማሳወቅ**
   1. .መድን ያልተገባለት ወይም ባልታወቀ ተሽከርካሪ የደረሰ አደጋን ተጎጂው ወይም የተጎጂው ቤተሰብ፤ የትራፊክ ፖሊስ ወይም ሌላ መንግስታዊ አካል፤ አደጋውን የሚያውቅ በአደጋው ቦታ የነበረ ማንኛውም ሰው ወይም የአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት የሰጠ ተቋም ወዲያውኑ ለፖሊስ ማሳወቅ አለበት፡፡
   2. የደረሰውን አደጋ ያወቀ ወይም እንዲያውቅ የተደረገ የትራፊክ ፖሊስ የትራፊክ አደጋን ለመመዝገብ በተዘጋጀው የመመዝገቢያ ስርዓት ወይም ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው ቅጽ በመሙላት ለአገልግሎቱ ማሳወቅ አለበት፡፡
   3. የተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን የመድን ውልና የካሳ አፈፃፀም መመሪያ አደጋን ስለማሳወቅ በተገለፀው መሠረት ለአገልግሎቱ ዋና መ/ቤት ወይም በየክልሉ ለተዋቀሩ የድህረ ትራፊክ አገልግሎት የስራ ክፍሎች በስልክ፣ በፋክስ ፣ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው መድን የሌለው ወይም ያልታወቀ ተሽከርካሪ የአደጋ ማሳወቂያ ወይም የትራፊክ ፖሊስ

የአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ ወይም በተዘረጋው የዲጂታል አሰራር ስርዓትን በመጠቀም ማሳወቁ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

7. **ከግዴታ ነፃ የሆነ ተሽከርካሪ ባለቤት**

   1. በአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን የመድን ውልና የካሳ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 656/2013 አንቀጽ 36 መሠረት የመከላከያ ሚኒስቴር የሚጠቀምበት ሆኖ በሀገር መከላከልና ደህንነት ተግባር በግንባር ቀጠና የተሰማራ ወይም ከዋናው መንገድ ውጭ የሚንቀሳቀስ ተሽከርካሪ ስላደረሰው አደጋ ተቋሙ ወይም አሽከርካሪው ወይም ፖሊስ ወይም ትራፊክ ፖሊስ ወይም ሌላ የሚመለከተው ሰው ማሳወቅ አለበት፡፡
   2. አደጋውን የማሳወቂያ መንገድ አገልግሎቱ ወይም በአገልግሎቱ የተወከለው አካል በሚያወጣው የመረጃ መላላኪያ ስርዓት ይሆናል፡፡

8. **የአደጋ መረጃ አሰባሰብ**

   1. በአዋጁ አንቀጽ 11 መሠረት መረጃ መስጠትን በተመለከተ መድን ገቢው የጉዳት ካሳ እንዲከፈለው ተጎጂው ወይም መብት ባለው ወገን ሲጠየቅ ተሽከርካሪው መድን ያለው ወይም የሌለው መሆኑንና መድን ምስክር ወረቀቱ ላይ በአዋጁ አንቀጽ 9 ላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች በመግለጽ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
   2. በአገልግሎቱ የተዘጋጀው እና በትራፊክ ፖሊስ ተሞልቶ በህክምና ተቋሙ የአስአቸኳይ ህክምና አገልግሎት እንዲሰጥ የሚተላለፈው የመጠየቂያ ቅጽ ወይም ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀ የዲጅታል አመዘጋገብ ስርዓት የተሞላ ፎርም እንደ አደጋ ማሳወቂያ እና የአደጋ መረጃ ምንጭ ሆኖ ሊወሰድ ይችላል፡፡
   3. ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አስቸኳይ ህክምና መጠየቂያ ቅጽ በትራፊክ ፖሊስ ሳይሞላ ቢቀር፤ አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት የሰጠው የህክምና ባለሞያ ወይም የአስቸኳይ ህክምና አስተባባሪው የሚሞላው የተሽከርካሪ አደጋ የህክምና ማስረጃ እንደ አደጋ ማሳወቂያ እና የአደጋ መረጃ ምንጭ ሆኖ ሊወሰድ ይችላል፡፡
   4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተሞላው ማስረጃ እንደ አደጋ ማሳወቂያ እና የአደጋ መረጃ ምንጭ ሆኖ ሊወሰድ የሚችለው ፎርሙን የሞላው ባለሞያ እና የህክምና ተቆሙ ኃላፊ ስምና ፊርማ፤ የህክምና ተቋሙ ማህተም እንዲሁም የደረሰውን አደጋ በአቅራቢያው ላለው የፖሊስ ተቋም በጽሁፍ ስለማሳወቁ ከሚያስረዳ ሰነድ ጋር ተያይዞ ሲቀርብ ነው፡፡

5. የትራፊክ ፖሊስ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ ወይም ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀ የዲጅታል አመዘጋገብ ስርዓት የተሞላ ፎርም መኖር መድን ላላቸው ወይም መድን ለሌላቸውና ገጭተው ላመለጡ እንዲሁም በአዋጁ ድንጋጌ ነፃ ለተደረጉ ተሽከርካሪዎች በሙሉ አደጋ ለማሳወቅና ክፍያ ለመጠየቅ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በመስጠት ያገለግላል፡፡

9. **የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ስለማግኘት**

1. .በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የሶስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ የአረቦን ተመን እና የካሳ ክፍያን ለመወሰን በወጣው ደንብ መሰረት በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው እስከ ብር 15000.00 ድረስ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት የማግኘት መብት አለው፡፡
2. በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ማንኛውም የህክምና ተቋም የተሽከርካሪ አደጋ ደርሶበት ወደ ህክምና ተቋሙ ለመጣ ለማንኛውም ተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
3. በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 ነጻ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት የሰጠ የህክምና ተቋም ለአገለልግሎቱ ያወጣውን ወጪ በዚህ መመሪያ ላይ በተገለጸው መሰረት እንዲከፈለው መጠየቅ ይችላል፡፡

10. **የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ዓይነት**

1. በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 16 መሰረት አስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ዓይነቶች

ሀ)በአደጋው ቦታ የሚደረግ የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና፣

ለ) ከአደጋው ቦታ ወደ ህክምና ተቋማት ተጎጂው በሚወሰድበት ወቅት የተሰጠ የአንቡላንስ አገልግሎትና በጉዞ ወቅት የሚደረግ የባለሙያ የህክምና አገልግሎት እና

ሐ) በህክምና ተቋም የድንገተኛ ክፍል (Emergency Ward (ED)) ውስጥ በባለሙያ የሚሰጥ የነፍስ አድን የህክምና አገልግሎት ነው፡፡

2. በህክምና ተቋም የድንገተኛ ክፍል (Emergency Ward (ED)) ውስጥ በባለሙያ የሚሰጥ የነፍስ አድን የህክምና አገልግሎት በሚከተሉት ሶስት ቦታዎች ሊሰጥ ይችላል፡-

ሀ) "The triage area"፣ ማለት የመጀመሪያ ደረጃ ምርመራ በህክምና ባለሙያ የሚደረግበት ቦታ

ለ) "The resuscitation area" ማለት የተለያዩ የነፍስ አድን ሥራዎች የሚካሄዱበት ቦታ፣

ሐ) "The major or general medical area" ማለት በድንገተኛ ክፍል በሚገኝ ተሽከርካሪ ጎማ ያለው አልጋ (Gurney) ወይንም ተጎታች ጋሪ (Trolley) ተጎጂው የሚያርፍበት ቦታ፡፡

3. የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ተጎጂው በሄደበት በየትኛውም ህክምና ተቋም ሊሰጥ ይችላል፡፡ ስለዚህ ተጎጂው የህክምና አገልግሎት ያገኘበት የመጀመሪያ የህክምና ተቋም እንደሰጠው አገልግሎት ክፍያ የመጠየቅ መብት አለው፡፡
4. የአስቸካይ ህክምና አገልግሎት የሰጠ እንድ የህክምና ተቋም ለአስቸካይ ህክምና ያወጣውን ወጪ ለመጠየቅ ተጎጂውን ተጨማሪ የአስቸካይ ህክምና እንዲያገኝ ወደ ሌላ የህክምና ተቋም ሲልክ የሰጠውን የአስቸካይ ህክምና አገልግሎት አይነት እና የወጣ ወጪ ዝርዝር አያይዞ ከተጎጂው ጋር መላክ አለበት፡፡
5. በድንገተኛ ክፍል ለተጎጂው ህክምና እየሰጠው ያለው የህክምና ባለሙያ ልዩ ህክምና እንዲያገኝ ወይንም በህክምና ተቋሙ ተኝቶ ወይንም በተመላላሽነት እንዲታከም ውሳኔ ሲሰጥ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎቱ ይቋረጣል፡፡
6. የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ወጪ ከአካል ጉዳት እና ከሞት ጉዳት ካሣ ላይ ተቀናሽ አይደረግም፤ ወይንም በጉዳት ካሣ ስሌት ውስጥ አይካተትም፡፡
7. በተሽከርካሪ አደጋ የተጎዳ ማንኛውም ሰው ከአደጋው ቦታ ወደ ህክምና ተቋማት የሚወሰድበትን የአንቡላንስ አጠቃቀም ስርአትን በተመለከተ የጤና ሚኒስቴር እና አገልግሎቱ በሚያጠኑት ጥናት ላይ ተመስርቶ በሚያወጡት የአተገባበር ማኑዋል መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**11. በአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ውስጥ የማይካተቱ ጉዳዮች**

1. ተጎጂው የላቀና ልዩ የህክምና አገልግሎት ወይም በህክምና ተቋሙ ወይም በሌላ ህክምና ተቋም በሪፈር ተኝቶ ወይም በተመላላሽነት በመታከሙ ምክንያት የወጣ የህክምና ወጪ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ባለመሆኑ ከአካል ጉዳት ወይም የሞት ካሳ ላይ ተቀንሶ የሚከፈል ይሆናል፡፡
2. በአዋጅ አንቀጽ 27 ንዑስ 4 እና አንቀጽ 24 መሠረት መድን ያልተገባለት ወይም ያልታወቀ ተሽከርካሪ ለሚያደርሰው ጉዳት የህክምና ተቋሙ ለህክምና አገልግሎት ያወጣውን ወጪ በቀጥታ ከፈንዱ እንዲከፈለው ለመጠየቅ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ መድን ባላቸው ተሽከርካሪዎች በደረሰ አደጋ የሚወጣውን የህክምና ወጪ ባለንብረት፣አሽከርካሪው፣ ተጎጂው፣ የተጎጂው ቤተሰብ ወይም ማንኛውም ሰው መክፈል ባይችሉ፤ ተጎጂው ወይም

ካሳ ሊቀበል የሚችል የተጎጂው ተወካይ ለህክምና የወጣውን ወጪ አገልግሎቱን የሰጠው ጤና ተቋም እንዲቀበል ፍቃዱን በጽሁፍ የሰጠ እንደሆነ፤ የህክምና ተቋሙ በቀጥታ መድን ሰጪው እንዲከፈለው ለመጠየቅ ይችላል፡፡

4. የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂ የህክምና ወጪ በሚከተሉት ወገኖች የሚሸፈን ይሆናል፡-
   ሀ. መድን ባላቸው ተሽከርካሪዎች በደረሰ አደጋ የመጣ ጉዳት ከሆነ የመድን ሽፋኑን በሰጠው የመድን ሰጪ ኩባንያ፣
   ለ. መድን በሌለውና ባልታወቀ ተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ከሆነ በአገልግሎቱ
   ሐ. በአዋጁ መሠረት የ3ኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ የመድን ሽፋን እንዲገቡ በማይገደዱ ተሽከርካሪዎች የደረሰ ጉዳት ከሆነ በተሽከርካሪው ባለንብረት ወይም በወኪሉ፡፡
5. ሌላ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና (ለ) ላይ ከተቀመጠው ኃላፊነት በላይ የሚመጣ ማንኛውም ዓይነት የጉዳት ካሳ በተሽከርካሪው ባለቤት ወይንም በኢትዮጵያ ሕግ ኃላፊነት በተጣለበት ወገን የሚሸፈን ወይንም የሚከፈል ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## የአገልግሎት ክፍያ አፈፃፀምና ተፈላጊ መረጃዎች

### 12. የአገልግሎት ክፍያ ስለመጠየቅ

1. በዚህ መመሪያ መሠረት ማንኛውም የህክምና ተቋም የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ ሊጠይቅ የሚችለው በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት በማንኛውም ሰው ላይ ለደረሰ ጉዳት ለተሰጠ አገልግሎት ብቻ ነው፡፡
2. ተጎጂው የተወሰደበት የህክምና ተቋም የሚሰጠው የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መፈፀም አለበት፡፡
3. ማንኛውም አስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የሰጠ የሕክምና ተቋም ክፍያ ሊጠይቅ የሚችለው የሚከተሉትን አካላትን ነው፡፡

ሀ. በሁሉም ክልሎች የሚገኙ የህክምና ተቋማት በተጨባጭ ባለው የክልሉ አወቃቀር ወይም አደረጃጀት መሰረት በዞን ወይም በወረዳ ባሉ ጤና ጽ/ቤቶች፤በከተማ መስተዳድሮች የሚገኙ ጤና ተቋማት በየክፍለ ከተማው ባሉ ጤና ጽ/ቤት ወይም በአስተዳደሩ ጤና ቢሮ ይጠይቃሉ፡፡

ለ.በፌዴራል መንግስት በሚገኝ ሆስፒታል እንዲሁም በየዩቨርስቲ ውስጥ ላሉ ሆስፒታሎች ለተሰጠ አስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የጤና ሚኒስቴርን ወይም በየዩቨርስቲው ክልል ጤና ቢሮ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

13. **ክፍያ ለመጠየቅ የተቀመጠ ቅድመ ሁኔታ**

አስቸካይ ህክምና አገልግሎት የሰጠ ማንኛውም ተቋም ለሰጠው አገልግሎት ክፍያ ለመጠየቅ፤

1. በዚህ መመሪያ ላይ የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች ሙሉ በሙሉ መከተል፣
2. በዚህ መመሪያ መሠረት የተዘጋጀውን የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ መጠየቂያ ቅጽ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎችን አያይዞ ማቅረብ፣
3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎቱ በሚያዘጋጀው የዲጂታል የአስቸኳይ ህክምና ክፍያ መጠየቂያ ስርዓት ላይ መረጃዎቹን በመሙላት ማያያዝ ይቻላል፡፡
4. ተጎጂው ህክምና በሚያገኝበት ተቋም ፤ የተጎጂው ህክምና ፋይል ውስጥ የሚከተሉት መረጃዎች ተደራጅተው ሊኖሩት ይገባል፡-

   ሀ. የተጎጂውን ስምና ሙሉ አድራሻ፣

   ለ. ተጎጂው በተሽከርካሪ አደጋ የተጎዳ መሆኑን በሚገኙ መረጃዎች ማጣራትና የአደጋውን ቀን፣የተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር፣ አደጋው የደረሰበትን ቦታ እና ሰዓት፣

   ሐ. ለአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ተጎጂውን ወደ ህክምና ተቋሙ የላከውን ትራፊክ ፖሊስ፣ ስምና ሙሉ አድራሻ፣ ታካሚው የተላከው በትራፊክ ፖሊስ ከሆነ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ እንዲቀርብ ማድረግና ማያያዝ፣

   መ. አደጋው የደረሰው መድን በገባ ተሽከርካሪ ከሆነ የመድን ሰጪው ኩባንያው ስምና የመድን የምስክር ወረቀት ቁጥር፣

   ሠ. አደጋው የደረሰው መድን በሌለው ተሽከርካሪ ከሆነ የተሽከርካሪውን ባለቤት ወይም የአሽከርካሪውን ስምና አድራሻ እንዲሁም የተሽከርካሪውን ሰሌዳ ቁጥር፣

   ረ. አደጋው የደረሰው ባልታወቀ ተሽከርካሪ ከሆነ ጉዳዩን የመዘገበው የትራፊክ ፖሊስ ወይንም ወደ ህክምና ተቋሙ ያመጣውን ሰው ስምና አድራሻ፣

   ሰ. ከላይ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከሀ እስከ ረ የተቀመጠው ቢኖርም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በትራፊክ ፖሊስ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ ሊሞላ ካልተቻለ የአስቸኳይ ህክምናውን የሰጠው ሀኪም ወይም የአስቸኳይ ህክምና

አስተባባሪው ተጎጂው ስለደረሰበት የትራፊክ አደጋ ለህክምና ተቋም በተዘጋጀው ቅጽ/ፎርም መሞላት እና የህክምና ተቋሙ መሀተም ማድረግ ይኖርበታል፣

5. አስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ በመጠየቂያ ቅጽ ተሞልቶ እና በሕክምና ተቋሙ ኃላፊ ተፈርሞ ለተጎጂው የተሰጠውን አገልግሎትና የወጪ ዝርዝር ከተፈላጊ ሰነዶች ወይም ማስረጃዎች ጋር በአግባቡ በመሙላት በአባሪነት ማያያዝና ማቅረብ ያለበት ሲሆን ከማስረጃዎቹ መካከልም እንደአግባብነቱ፣
   ሀ. የሀኪም ትዕዛዝ፣ የሀኪም አስፈላጊ መረጃ፣ ደረሰኝ የመድሀኒት ወይንም የላብራቶሪ ምርመራ ክፍያና ሌሎች ሰነዶችን፣
   ለ. የትራፊክ ፖሊስ ሪፖርት፣ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ፣ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ መጠየቂያ ቅጽ የተሳከ ከሆነ እና የትራፊክ ፖሊስ የአደጋ ሪፖርት ወይም የትራፊክ ፖሊስ ሪፖርት በማይገኝበት ሁኔታ በጤና ተቋሙ የሚሞላ መረጃ ናቸው።

14..የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄ አቀራረብና የአፈፃፀም ሥርዓት

1. ማንኛውም የህክምና ተቋም አገልግሎት የሰጠበት ወር ባለቀ 10 ቀን ውስጥ እንደየ ክልሉ አደረጃጀትና አወቃቀር ሁኔታ ለዞን ጤና መምሪያ፣ለወረዳ ፣ለክፍለ ከተማ ጤና ጽ/ቤት ወይም እንደ ክልሉ የህክምና ተቋማት ተጠሪነት ለክልሉ ጤና ቢሮ የክፍያ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል።
2. የህክምና ተቋሙ የክፍያ ጥያቄው እና አባሪ ሰነዶች የሚያቀርቡት ለዚሁ ተግባር ተብሎ በተዘጋጀው የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ መጠየቂያ ፎርም ሲሆን አስፈላጊ መረጃዎችን በመሙላት እና በማጠቃለል በእያንዳንዱ ሰነድ ላይ የህክምና ተቆሙ የኃላፊ ፊርማና ማህተም መኖር አለበት።
3. ከተገለፀው የ10 ቀን የጊዜ ገደብ ካለፈ በኂላ በተንጠባጠበ መንገድ የሚቀርቡ የክፍያ ጥያቄዎችና አባሪ ሰነዶች ሊስተናገዱ የሚችሉት በሚቀጥለው ወር ይሆናል። ሆኖም ግን ክፍያው በበጀት አመቱ ካለቀ በኃላ እስከ ሶስት ወር ድረስ ብቻ የሚስተናገድ ይሆናል።
4. እያንዳንዱ የዞን ጤና መምሪያ፣ የወረዳ ወይም የክፍለ ከተማ ጤና ጽ/ቤት በአካባቢው ከሚገኙ የህክምና ተቋማት የቀረበለትን የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄ ሰነዶችን ማጣራት ካደረገ በኂላ ሰነዶቹን በአግባቡ በማስቀመጥ በተጠቃለለ ሪፖርት ሰነዶቹ በደረሱት በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ክፍያው አገልግሎት በሰጠው ተቋም ስም እንዲፈፀም ለክልል/ለከተማ መስተዳደሩ የጤና ቢሮ ጥያቄ ማቅረብ አለበት።

5. እንደ አግባብነቱ የክልል ጤና ቢሮዎች አደረጃጀት እና አወቃቀር እያንዳንዱ ዞን ጤና መምሪያ ወይም የወረዳ ወይም ክፍለ ከተማ ጤና ጽ/ቤት የሚከተሉትን የማጣራት ተግባር ያከናውናል፤

   ሀ. የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄውና በአባሪነት የተያያዙት ሰነዶች ትክክለኛነት፣

   ለ. የክፍያው ጥያቄ አቀራረብ በዚህ መመሪያ ላይ በተዘረዘረው መሠረት እንደሆነ እና

   ሐ. ከህክምና ተቋማት የቀረበለትን የእያንዳንዱ ተጎጂን የአስቸካይ ህክምና አገልግሎት ከክፍያ ጣሪያ በላይ አለመሆኑን ያጣራል፡፡

6. እንደ አግባብነቱ የክልል ጤና ቢሮዎች አደረጃጀት እና አወቃቀር እያንዳንዱ ዞን ጤና መምሪያ ወይም የወረዳ ወይም የክፍለ ከተማ ጤና ጽ/ቤት አጠራጣሪ እና ያልተሟላ መረጃ ያለው የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የክፍያ ጥያቄ ከሆነ ደግሞ ሁኔታውን ዘርዝሮ በመግለጽ ሰነዱን ለሚመለከተው የህክምና ተቋም ወዲያውኑ በሸኚ ደብዳቤ ተመላሽ ያደርጋል፡፡

7. ለክልሉ ጤና ቢሮ ተጠሪ ለሆኑ የህክምና ተቋማት በተመሳሳይ ሁኔታ ክልል ውስጥ ከሚገኙ የሕክምና ተቋማት የቀረበላቸውን የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄና አባሪ ሰነዶችን በማጣራት ተገቢውን ክፍያ በ10 የሥራ ቀን ውስጥ መፈፀም ያለባቸው ሲሆን፣

   ሀ. የሚጣሩት ጉዳዮች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14/5/ ስር የተገለፁት ተግባራት መሟላታቸውን ማረጋገጥ፣

   ለ. አጠራጣሪና ያልተሟላ መረጃ ያላቸው የክፍያ ጥያቄዎች ለሚመለከተው የጤና ተቋም በሸኚ ደብዳቤ አማካኝነት በዚሁ የጊዜ ገደብ ውስጥ አስተካክለው እንዲያቀርቡ መላክ አለባቸው፡፡

## 15. የክልል ወይም የከተማ አስተደደር የጤና ቢሮ ተግባር

1. እንደየ ክልሉ አደረጃጀት እና አወቃቀር ሁሉም ክልል እና የከተማ መስተዳድር ጤና ቢሮ ከዞን፣ ከወረዳ ወይም ከክፍለ ከተማ ጤና ጽ/ቤት የቀረበላቸውን የተጠቃለለ የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄ በማጣራት በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ክፍያውን መፈፀም አለባቸው፡፡
2. የክልሉ ጤና ቢሮ ተጠሪ ከሆነባቸው የህክምና ተቆማት በቀጥታ የቀረበለትን የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄ ሰነዶችን በማጣራት ተገቢውን ክፍያ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ መፈጸም አለበት፡፡

3. በዚህ መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት የተፈፀመ እያንዳንዱ የአገልግሎት ክፍያ፣ ክፍያው በተፈጸመ በ10 የስራ ቀናት ውስጥ የከፈለበትን ዝርዝር ሪፖርት በማያያዝ በሸኚ ደብዳቤ ለጤና ሚኒስቴር መላክ አለበት፡፡

16. **የጤና ሚኒስቴር ተግባር**

የጤና ሚኒስቴር በስሩ ለሚተዳደሩ የህክምና ተቋማት የህክምና አገልግሎት የሰጡበትን አባሪ ሰነዶችን በህክምና ተቋሙ እንዲደራጁ በማድረግ ከተቋሙ በቀረበለት የተጠቃለለ የአገልገሎት ክፍያ መጠየቂያ ሪፖርት መሰረት በ10 የስራ ቀናት ውስጥ ለህክምና ተቋማቱ ክፍያ መፈጸም አለበት፡፡

17.**ሪፖርት ስለመላክ**

1. እንደ ክልሉ አደረጃጀት እና አወቃቀር መሰረት የዞን ጤና መምሪያ ወይም የወረዳ ወይም የክፍለ ከተማ ጤና ጽህፈት ቤቶች ወሩ ባለቀ በ10 የስራ ቀናት ውስጥ የአገልግሎት ሪፖርት እና የፋይናንስ ሪፖርት አጠናቅሮና አዘጋጅቶ ለክልሉ ጤና ቢሮ መላክ አለበት፡፡
2. ሁሉም ክልል እና የከተማ መስተዳድር የጤና ቢሮ በየወሩ የተከፈሉ የአገልግሎት ክፍያ መግለጫ ሪፖርት እንደ ክልሉ አደረጃጀት እና አወቃቀር ከዞን ጤና መምሪያዎች ፣ ወረዳዎቹ ወይም ክፍለ ከተማው በደረሰው በ10 ቀናት ውስጥ በማደራጀት ለጤና ሚኒስቴር መላክ አለበት
3. የጤና ሚኒስቴር እራሱ የአገልግሎት ክፍያ የፈፀመባቸውን እንዲሁም በክልል ወይም በከተማ አስተደደር የጤና ቢሮ ክፍያ ስለመፈፀሙ ሪፖርት በደረሰው ወር ባለቀ በ10 የስራ ቀናት ውስጥ በማጣራትና በመለየት የአገልግሎት ክፍያ መግለጫ ሪፖርቱን ለአገልግሎቱ መላክ አለበት፡፡
4. አገልግሎቱም ከጤና ሚኒስቴር የተላከለትን የአገልግሎት ክፍያ መግለጫ ሪፖርት በማጠናቀር በየሩብ አመቱ በሚዘጋጀው የጋራ ምክክር ፎርም ላይ ለባለድርሻ አካላት ያቀርባል፡፡

# ክፍል አራት

# የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ፈንድ ማቋቋምና ማስተዳደር

**18.መቋቋም**

የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ፈንድ ከዚህ በኋላ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ፈንድ እየተባለ የሚጠራ የገንዘብ ምንጭ በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፡፡

**19.የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ፈንዱ አላማ**

የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ፈንድ አላማ በተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 27 የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ድንጋጌዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ነው፡፡

**20. የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ፈንድ ምንጭ**

የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ፈንድ የሶስተኛ ወገን የመደን ሽፋን ከሚሰጡ መድን ሰጭ ኩባንያዎች እንዲሁም ከአገልግሎቱ የሚሰበሰብ መዋጮ ነው፡፡

**21. የአስቸካይ ህክምና አገልግሎት ፈንድ መጠንና ድርሻ አወሳሰን**

1. የአስቸካይ ህክምና አገልግሎት ፈንድ መጠን የሚወሰነው በሦስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ የመድን ፖሊሲ የአረቦን ተመን እና የካሳ መጠን ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 554/2016 መሰረት መሠረት ነው፡፡
2. የእያንዳንዱ መድን ሰጪ ኩባንያ እና የአገልግሎቱ የመዋጮ ድርሻ መጠን የሚወሰነው በሦስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ የመድን ፖሊሲ የአረቦን ተመን እና የካሳ መጠን ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 554/2016 መሰረት ሲሆን የመድን ሰጪ ኩባንያዎች እና የአገልግሎቱ የመዋጮ ድርሻ መጠን የሚሰላው ከሚሰበስቡት የሶስተኛ ወገን መድን ሽፋን አረቦን ታሪፍ እንዲሁም የመድን ፈንድ ታሪፍ ላይ ተመርኩዞ ይሆናል፡፡
3. በዚህም መሰረት የመድን ሰጪ ኩባንያዎች የአስቸካይ ህክምና አገልግሎት ፈንድ የመዋጮ ድርሻ የሶስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ የመድን ዋስትና የአረቦን መጠን ላይ 3% (ሶስት በመቶ) እንዲሁም አገልግሎቱ ከመድን ሰጪዎች ከሚሰበስበው የፈንድ ታሪፍ ላይ 3% (ሶስት በመቶ) ይሆናል፡፡

**22. የመዋጮ መጠንና ደርሻን ስለማሳወቅ**

አገልግሎቱ ባካሄደው ጥናት መሰረት በሦስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ የመድን ፖሊሲ የአረቦን ተመን እና የካሳ መጠን ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 554/2016 በስራ በዋለ በ3 የስራ ቀናት ውስጥ ለሚመለከታቸው አካላት በጽሁፍ ወይም በማንኛውም መረጃ ማስተላለፊያ መንገድ ያሳውቃል፡፡

## 23. የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ፈንድ የመዋጮ መጠን አሰባሰብ

1. የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ፈንድ የመዋጮ ድርሻ ገቢ የሚደረጉ ክፍያዎች በአገልግሎት ስም በሚከፈት የባንክ ሂሳብ ሆኖ በአገልግሎቱ አማካኝነት ለዚሁ ተብሎ በጤና ሚኒስቴር በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ ይደረጋል፡፡
2. የአረቦን መጠን እና የመድን ፈንድ ታሪፍ በሦስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ የመድን ፖሊሲ የአረቦን ተመን እና የካሳ መጠን ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 554/2016 መሠረት በመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ውስጥ እ.ኤ.አ(Gregorian calander) የቀን አቆጣጠር በየወሩ ሆኖ እያንዳንዱ ወር ካበቃ በኋላ ባለው ቀጣይ ወር መጨረሻ ቀን ድረስ ሁሉም መድን ሰጭ ኩባንያዎች ገቢ ማድረግ አለባቸው፡፡ የቀጣዩ ወር የመጨረሻ ቀን እሁድ ወይም የበዓል ቀን ከሆነ የመጨረሻው ቀን ቀጣዩ የስራ ቀን ይሆናል፡፡ ሆኖም አገልግሎቱ ዲጅታላይዝ አቦን አሰባሰብ ስልት የሚጠቀም ከሆነ የአሰባሰቡ ሁኔታ ከዚህ የተለየ የአሰራር ስርዓት ይኖረዋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) በተጠቀሰው የክፍያ ወቅት ውስጥ የተሰበሰበውን የአስቸካይ ህክምና አገልግሎት ተዘዋዋሪ ፈንድ ድርሻ ገቢ ያላደረገ የመድን ሰጭ ኩባንያ ክፍያውን ላዘገየበት ጊዜ በዘገየው የገንዘብ መጠን ላይ በኢትየጵያ የፍትሀብሄር ህግ ወስጥ የተደነገገውን ህጋዊ ወለድ ጨምሮ በአገልግሎቱ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ ሆኖም አገልግሎቱ ዲጅታላይዝ አርቦን አሰባሰብ ስልት የሚጠቀም ከሆነ የአሰባሰቡ ሁኔታ ከዚህ የተለየ የአሰራር ስርዓት ይኖረዋል፡፡

## 24.የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ፈንድ ስርጭት እና አጠቃቀም

1. እያንዳንዱ ክልል እና ከተማ መስተዳድር ጤና ቢሮ 75% የአስቸይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ ጥቅም ላይ የዋለ መሆኑን መረጃዎች ከጠቆሙ ጤና ሚኒስቴር ለቀረው ግዜ የሚሆን ፈንድ እንዲመደብ ለአገልግሎቱ ያሳውቃል፡፡

2. በዚህ መንገድ በክልል እና በከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮዎች ስም ተሰልቶ የሚመደበው የአስቸካይ ህክምና አገልግሎት የፈንድ ድርሻ ተቀማጭ የሚሆነው በሚመለከተው የጤና ቢሮ ስም ለዚሁ ተብሎ በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ነው፡፡
3. እንደ ክልሉ አደረጃጀት እና አወቃቀር በእያንዳንዱ ዞን ፣ ክፍለ ከተማ  አስተዳደር ወይም ወረዳ ሥር ባሉ የሕክምና ተቋማት የአገልግሎት ክፍያ ሲፈፀም በክልሉ ወይም በከተማ አስተዳደሩ ጤና ቢሮ የባንክ ሂሳብ ለወቅቱ ከተመደበለት ገንዘብ ይቀነሳል፡፡
4. በክልል ወይም በከተማ አስተዳደሩ ያሉ ጤና ቢሮ ከተመደበለት የፈንድ ድርሻ በላይ ለመጠቀም የክፍያ ጥያቄ ከቀረበ ጉዳዩን ለክልሉ የጤና ቢሮ እና ለጤና ሚኒስቴር በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

25. **የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ፈንድ ኦዲት ስለማድረግ**

1. .ያአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ፈንድ የሂሳብ ዘመን በየአመቱ ከሀምሌ 1 ቀን በመጀመር እስከ ሰኔ 30 ድረስ ይሆናል፡፡
2. የሂሳብ ምዝገባ ሥርዓት በመንግስት የፋይናንስ ስርዓት መሆን አለበት፡፡
3. የጤና ሚኒስቴር የበጀት ዓመቱ ባለቀ በሁለት ወር ውስጥ የክልል እና የከተማ መስተዳደር ጤና ቢሮዎችን እና በስሩ የሚተዳደሩ የህክምና ተቋማትን የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ በትክክል መጠቀማቸውን በውስጥ እና በውጪ ኦዲተር ኦዲት ያስደርጋል፡፡
4. የኦዲት ሪፖርቱ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲሁም ለመንገድ ደህንነት እና መድን ፈንድ አገልግሎት ቦርድ ቀርቦ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የባለድርሻ አካላት በተገኙበት የጋራ ውይይት ይደረግበታል፡፡
5. የኦዲት ሪፖርቱ ለመጪው ዘመን የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ፈንድ ትመናና መሠረታዊ ግብዓት በመሆን ያገለግላል፡፡

## ክፍል አምስት

## የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 26.የመንገድ ደህንነት እና መድን ፈንድ አገልግሎት

በደንብ ቁጥር 493/2014 ላይ ለአገልግሎቱ ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች በተጨማሪ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡ እነሱም፡-

1. የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት አፈፃፀም መመሪያውን ተግባራዊነት የሚያረጋግጥ እና የሚቆጣጠር ይሆናል፡፡
2. በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች በዚህ መመሪያና በአዋጁ መሰረት የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ማግኘታቸውን ይገመግማል እንዲሁም የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂዎችን ቅሬታ ተቀብሎ ውሳኔዎች ይሰጣል፡፡
3. በአሰራር ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን በመገምገም ማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 30 መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ ለተቋሙ ያቀርባል፡፡
4. ለአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የተመደበው ገንዘብ በአዋጁና በዚህ መመሪያ ላይ በተዘረዘረው መሰረት በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤ ያጋጠሙ ችግሮችና የተገኙ ውጤቶችን በየሩብ ዓመቱ ያቀርባል፡፡
5. የትራፊክ ፖሊስ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የመጠየቂያ፣ የትራፊክ ፖሊስ የአደጋ ሪፖርት መስጫ፣እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶችና ቅፆችን በማዘጋጀትና በማሳተም ያሰራጫል ወይም በዲጂታል የአመዘጋገብ ስርዓትን ያስተዋውቃል እንዲሁም ስለአጠቃቀሙ ግንዛቤ ይሰጣል፡፡
6. .የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የክፍያ መጠየቂያ ፎርም በሶፍት ኮፒ በማዘጋጀት በጤና ሚኒስቴር በኩል ለህክምና ተቋማት እንዲደርሰቸው ያደርጋል እንዲሁም ይከታተላል፡፡
7. አገልግሎቱ የጤና ሚንስቴር የአስቸይ ህክምና አገልግሎት አፈጻጸማቸውን በመገምገም እና በማጥናት የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ፈንድ መጠን ውሳኔ እንዲሻሻል ለቦርድ ያቀርባል ሲወሰንም ለሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊ የመረጃ መለዋወጫ ዘዴ በመጠቀም ያሳውቃል፡፡
8. የአስቸካይ ህክምና አገልግሎት ፈንድ ለመድን ሰጪዎች የመዋጮ ድርሻ የሶስተኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ የመድን ዋስትና የአረቦን መጠንና የመድን ፈንድ ታሪፍ በተጠናውና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሀምሌ 2016 ዓ.ም በፀደቀው መሰረት 3% የመዋጮ ድርሻ ከመድን ሰጪዎች ይሰበስባል፡፡

9. አስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ መረጃ የሚያዝበትን ዲጂታል መረጃ አያያዝ ስርዓት ይዘረጋል ያዘጋጃል፤ ሌሎች የኦዲት ሰነዶችን በአግባቡ ይይዛል፡፡
10. ድህረ ትራፊክ አገልግሎትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ አሰራሮችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር የአተገባበር ስልት ይቀይሳል፡፡
11. አስቸኳይ ህክምናን በተመለከተ የግንዛቤ፣ የኢንስፔክሽን እና ድጋፍ እና ክትትል ስራ ከባለድርሻ አካላት ጋር ይሰራል፡፡

27. **የመድን ሰጪ ኩባንያዎች**

1. ለአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ የሚሆን መዋጮ (የአስቸካይ ህክምና አገልግሎት ፈንድ ድርሻ) አገልግሎቱ በዘረጋው በዲጂታል አመዘጋገብ ስርዓት በሚጠይቀው በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ ያደርጋል፡፡
2. አስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ፈንዱን በትክክል ገቢ የማያደርጉ መድን ሰጪ ኩባንያዎችን ገንዘቡን ከነወለዱ ገቢ እንዲያደርጉ ያደርጋል፡፡ሆኖም አገልግሎቱ ዲጅታላይዝ አርቦን አሰባሰብ ስልት የሚጠቀም ከሆነ የአሰባሰቡ ሁኔታ ከዚህ የተለየ የአሰራር ስርዓት ይኖረዋል፡፡
3. በተከፈተው የሂሳብ ቁጥር ገቢ ያደረጉትን ገንዘብ መጠን የሚያሳይ የባንክ ደረሰኝ ኮፒ ለአገልግሎቱ ይልካሉ ወይም ያሳውቃሉ፡፡ሆኖም አገልግሎቱ ዲጅታላይዝ አርቦን አሰባሰብ ስልት የሚጠቀም ከሆነ የአሰባሰቡ ሁኔታ ከዚህ የተለየ የአሰራር ስርዓት ይኖረዋል፡፡

28.**የጤና ሚኒስቴር**

1. በዚህ መመሪያ በተገለጸው መሰረት ለአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት ክፍያ የሚሆን መዋጮ የሚመሰረተውን ለአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት ፈንድ የሚቀመጥበትን የባንክ ሂሳብ በመክፈት ቁጥሩን ያሳውቃል፤ ለክልል እና ለከተማ አስተዳደሮች የጤና ቢሮዎች ያስተዳድራል፡፡
2. ክልልና ከተማ መስተዳድር ጤና ቢሮ የከፈሉትን የአፈጻጸም ሪፖርቶችን ከሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ይሰበስባል እንዲሁም ክፍያውን የሚገልጽ ሪፖርቶችን በየወሩ ለአገልግሎቱ ያቀርባል፡፡
3. ለተሽከርካሪ አደጋ አስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የተመደበውን ክፍያዎች በውስጥና በውጪ ኦዲተር ኦዲት ያስደርጋል፡፡

4. የተሸከርካሪ አደጋ አስቸኳይ ህክምናን በተመለከተ ሀሰተኛ በሆኑ ማስረጃዎች በህክምና ተቋሙ ነፃ አስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ሰጥቶ ከተገኘ በህክምና ተቋሙ እንዲሁም በሰራተኛው ላይ በሚኒስቴሩ የመተዳደርያ ህግ መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡
5. ጤና ሚኒስትሩ የሚያስተባብራቸው ሁሉም ባለድርሻ አካላት አሰራሩን ተግባራዊ እንዲያደርጉ የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ከአገልግሎቱ ጋር በጋራ ይሰራል፣
6. በየሩብ አመቱ ስለስራ አፈፃፀሙ የስራ ግምገማ ያደርጋል፤ ውጤቱንም ለባለድርሻ አካላት ከአገልግሎቱ ጋር በመሆን ያቀርባል፣

## 29.የጤና ቢሮ

1. እንደየ ክልሉ አደረጃጀት ከዞን ወይም ከወረዳ ከክፍለ ከተማ ጤና ጽ/ቤት ተጣርቶ የቀረበለትን የአገልግሎት ክፍያ ሪፖርቶችን አጣርቶ በዚህ መመሪያ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በህክምና ተsሙ ስም ክፍያ ይከፍላል፡፡
2. እንደየ ክልሉ አደረጃጀት ለክልል ጤና ቢሮ በቀጥታ ተጠሪ ለሆኑ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ሰጪ የህክምና ተቋማት የተላከለትን የወጭ ሰነድ አጣርቶ በዚህ መመሪያ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ክፍያ እንዲከፈል ያደርጋል፡፡
3. ለተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂዎች ፎካል ፐርሰን (ተወካይ) ለህክምና ተ□ማት እንዲመደቡ ያደርጋል፡፡
4. የየወሩን የአገልግሎት ክፍያ የአፈፃፀም መግለጫ ሪፖርት በማዘጋጀት ለጤና ሚኒስቴር በዚህ መመሪያ ላይ በተገለጸው ጊዜ ይልካል፡፡
5. በሀገሪቱ ውስጥ ያለ ማንኛውም ህክምና ተቋም በመንገድ ላይ አደጋ ተጎጂ ለሆነ ማንኛውም ሰው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት እንዲሰጥ በአዋጁ የተቀመጠውን ድንጋጌ እና ይህን መመሪያ ተግባራዊ እንዲያደርጉ በስሩ ያሉትን የህክምና ተቋማት ይቆጣጠራል፡፡

## 30.እንደ ክልሉ አደረጃጀት የዞን/ የክፍለ ከተማ/.የወረዳ ጤና ጽ/ቤት

1. ከጤና ተቋማት የሚመጡ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ጥያቄ ሰነዶችን አጣርቶ በተጠቃለለ የአፈጻጸም ሪፖርት ለክልል ጤና ቢሮ በህክምና ተsሙ ስም ክፍያ እንዲከፈል ጥያቄ ያቀርባል፡፡
2. በሀገሪቱ ውስጥ ያለ ማንኛውም ህክምና ተቋም በመንገድ ላይ አደጋ ተጎጂ ለሆነ ማንኛውም ሰው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት እንዲሰጥ

በአዋጁ የተቀመጠውን ድንጋጌ እና ይህን መመሪያ ተግባራዊ እንዲያደርጉ በስሩ ያሉትን የህክምና ተቋማት ይቆጣጠራል፡፡

31..የሕክምና ተቋማት

1. እስከ ብር 15,000.00 (አስራ አምስት ሺህ) ድረስ በነፃ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለባቸው፣
2. የህክምና ተቋማት ለተገልጋዩ በግልፅ በሚታይ ቦታ ላይ አስቸ�ይ ህክምና አገልግሎት ነፃ መሆኑን የሚገልፅ ቢል ቦርድ መስቀል አለባቸው፡፡
3. የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎትክፍያ መጠየቂያ ቅጽ በመጠቀምና አባሪ ሰነዶችን በማያያዝ ወይም በዲጂታል የአመዛዘገብ ስርአት በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ለህክምና ያወጡት ወጪ እንዲከፈላቸው ለወረዳ የጤና ጽ/ቤት ማቅረብ አለባቸው፡፡
4. በዚህ መመሪያ ተጠቀሱትን ተፈላጊሆኑ መረጃዎችን ማሰባሰብ አለባቸው፡፡
5. የአስቸኳይ ህክምና መረጃ መስጫ ቅጽ ሣይኖር ወደ ህክምና ተቋም የሚመጡ ተጎጂዎች በህክምና ምርመራ ውጤቶች የትራፊክ አደጋ ስለመሆኑ ያረጋግጣል፡፡
6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት በህክምና ባለሙያው እና በህክምና ተቋሙ ሀላፊ ፊርማ የተረጋገጠ የህክምና ማረጋገጫ መረጃ ውሳኔ እንዲሁም በህክምና ተቋሙ ማህተም የትራፊክ አደጋ ስለመሆኑ ያረጋግጣል፡፡
7. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 5 መሰረት የህክምና ተቋሙ በትራፊክ የሚሞላው አስቸኳይ ህክምና መረጃ መስጫ ቅጽ/ፎርም ሣይኖረው ለተጎጂው ስለሰጠው ህክምና በአቅራቢያው ለአለው የፖሊስ መምሪያ በጹሑፍ ወዲያውኑ ያሳውቃል፡፡
8. በተሽከርካሪ ጉዳት የደረሰበት ተጎጂ ከአደጋ ቦታ እስከ ህክምና ተቋም በአንቡላንስ የመጣ ከሆነ ህክምና ተቋማት ማረጋገጫ መስጠት አለባቸው፡፡
9. ታካሚው በህክምና ተቆም ውስጥ ተኝቶ ወይም በተመላላሽነት እንዲታከም የህክምና ባለሙያው ውሳኔ ሲሰጥ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎቱ ይቋረጣል፣ቀጣይ ህክምናን በተመለከተ ተጎጂው እና የጤና ተቋሙ ከአገልግሎቱ ወይም ከሌሎች መድን ሰጪዎች ጋር በመግበቢያ ሰነድ ስምምነት የሚቀጥል ይሆናል፡፡
10. በተሽከርካሪ አደጋ በሪፈር ተጎጂዎች ወደ ሌላ ጤና ተቆም በሚላኩበት ጊዜ አስፈላጊ የህክምና መረጃዎችን ያወጡትን ወጪ የሚገልጹ መረጃ ኮፒ እንዲያያዙ ማድረግ አለባቸው፡፡

11.ሪፈራል ተብለው የመጡ የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መቀበል አለባቸው፡፡

32.ፖሊስ ወይም የትራፊክ ፖሊስ

1. ማንኛውም የትራፊክ ፖሊስ የተሽከርካሪ አደጋ በደረሰ ጊዜ በአገልግሎቱ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ወይም በድጂታል የአመዘጋገብ ስርዓት ተጎጂው ወደ ህክምና ተቋም እንዲሄድ ያደርጋል፡፡
2. ለተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂዎች ፎካል ፐርሰን (ተወካይ) በፖሊስ ተ□ማት እንዲመደቡ ያደርጋል፡፡
3. የተሽከርካሪ አደጋ በደረሰ ጊዜ በቦታው ወይም በስፍራው የትራፊክ ፖሊስ ሳይኖር ተጎጂው ወደ ህክምና ተቋም የተወሰደ ከሆነ ፖሊስ የተሽከርካሪ አደጋ መድረሱን አጣርቶ ለህክምና ተቋሙ ማሳወቅ ይኖርበታል፣
4. ትራፊክ ፖሊስ ከማንኛውም የህብረተሰብ አካል ለደረሰው የተሽከርካሪ አደጋ ጥ□ማ አጣርቶ ማረጋገጥ አለበት፡፡
5. በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 7 መሰረት የህክምና ተsሙ አገልግሎት ስለሰጠው የተሽከርካሪ አደጋ ስለደረሰበት ተጎጂ መረጃ የማጣራት ግዴታ አለበት፡፡

33.ሌሎች አካላት

ተጎጂው ወይም የተጎጂ ቤተሰቦች ፣ ማንኛውም የህብረተሰብ አካል ፣መድን የገባውሰው፣የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም አስተዳዳሪ ወይም አደጋውን ያደረሰው አሽከርካሪ፣ ስለአደጋው እንደሁኔታው ለአገልግሎቱ ወይም ለመድን ሰጭ ኩባንያው በ10 ቀናት ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ

34. ቅሬታ አቀራረብ

1. ማንኛውም የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበት የህክምና ተቋም ወይም ጉዳት የደረሰበት ሰው በዚህ መመሪያ በተገለፀው አሰራር መሰረት ባይፈፀምለት እና ቅሬታ ቢኖረው ቅሬታውን ለድህረ ትራፊክ አደጋመድን አገልግሎት መሪ ስራ አስፈፃሚ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. የድህረ ትራፊክ አደጋ መድን አገልግሎት መሪ ሥራ አስፈፃሚ ለቀረበው ቅሬታ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡
3. በመሪ ስራ አስፈፃሚው ምላሽ ቅሬታ ያለው ሰው ቅሬታውን በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለአገልግሎቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ማቅረብ ይችላል፡፡
4. የአገልግሎቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ለቀረበው ቅሬታ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡
5. በዋና ስራ አስፈፃሚው ለቅሬታ አቅራቢው የሚሰጠው ምላሽ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል፡፡

35. የተሻረ መመሪያ

የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎትን በተመለከተ ከዚህ በፊት የወጣው የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 655/2013 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

36. .መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ድህረ ገጽ ላይ ሲጫን ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 40. አባሪዎች

ትራፊክ ፓሊስ
የድንገተኛ /አስቸኳይ/ ህክምና አገልግሎት
መረጃ መስጫ ቅጽ

ቀን ____________

No. 07501

1. የተጎጂው ሙሉ ስም ____________
2. የተሽከርካሪው አይነት እና ሰሌዳ ቁጥር ____________
3. የአሽከርካሪው ሙሉ ስም ____________
4. አደጋው የደረሰበት ቦታ /ቀን/ ሰዓት ____________
5. ተጎጂው የተላከበት የህክምና ተቋም ስም ____________
6. ትዕዛዙን የሰጠው የትራፊክ ፓሊስ ____________
   - ሙሉ ስም ____________
   - የፓሊስ ጣቢያው ስም ____________
   - አድራሻ፣ ክልል ________ ክ/ከተማ/ዞን ______ ወረዳ ______ ቀበሌ ______
     የስልክ ቁጥር ____________ ሞባይል ቁጥር ____________
   - ፊርማ ____________

<u>ማስታወሻ</u>፣ ይህ ቅጽ ለመድን ፈንድ ጽ/ቤት እንደ አደጋ ማሳወቂያ ያገለግላል
በ2 ኮፒ የሚዘጋጅ ሲሆን

- ✓ ዋናው ለህክምና ተቋሙ
- ✓ ቀሪው በትራፊክ ጽ/ቤት ይቀመጣል

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- ይህ ቅጽ የደረሰው የጤና ተቋም ለተጎጂው የአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበት ሲሆን ክፍያውን የሚመለከተውን አካል የመጠየቅ መብት አለው።

National Printing Press PLC

## በፖሊስ ተቋማት የሚሞላ የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጅ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ

……………ቀን20…………ዓ.ም 2015/ስሪ/ቀ **№ Ͻ004101**

ለ………………………………………………………………………

(ለመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት /ለመድን ሰጭዉ ኩባንያ/)

1. አደጋዉን ያደረሰዉ አሽከርካሪ የሚታወቅ ከሆነ

ሀ. ሙሉ ስም ……………………………………………………………………

ለ. የመንጃ ፈቃድ ቁጥር ……………………………………ደረጃዉ ………………………

ሐ. አድራሻ፡- ክልል…………ክ/ከ…………ዞን…………ወረዳ………ቀበሌ……የቤት ቁ………………

መ. የሞባይል ቁጥር………………………

ሠ. አደጋ አድራሹ አሽከርካሪ የማይታወቅ ከሆነ ይገለጽ………………………………………………

2. አደጋ ያደረሰዉ ተሽከርካሪ የሚታወቅ ከሆነ

ሀ. የሰሌዳ ቁጥር……………………………………………………

ለ. የተሽከርካሪዉ አይነት ……………………………………………

ሐ. የተሽከርካሪዉ ባለቤት ሙሉ ስም…………………………………

- አድራሻ፡- ክልል…………ክ/ከ…………ዞን………ወረዳ…………ቀበሌ………የቤት ቁ…………………

- የሞባይል ቁጥር………………………

መ. የመድን ምስክር ወረቀት የመድን ተሰጣሬ ቁጥር……………………

- የዉል ዘመን ከ………………………እስከ………………………

- የመድን ሰጭዉ ኩባንያ ስም ……………………………………………

- ቅርንጫፍ ……………………………………………………

3. የአደጋዉ መንስኤ ……………………………………………………

4. የተሽከርካሪዉ ዝርዝር መረጃ

ሀ. አደጋዉ የደረሰበት ቀን ……………………ቦታ ……………………ሰዓት……………………

ለ. የአደጋዉ አይነት ……………………………………………………………………

5. . በደረሰዉ የተሽከርካሪ አደጋ ጉዳት የደረሰባቸዉ ተጎጅዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የተጎጂ ስም | ተሳፋሪ /መንገደኞች/ ሹፌር ረዳት ወዘተ | የጉዳቱ ዓይነት ቀላል/ከፍተኛ /ሞት | የተጎጂ አድራሻ | የተጎጂ /ቤተሰብ ስልክ | የተሳከበት ህክምና ተቋም ስም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | | | |
| 2 | | | | | | |
| 3 | | | | | | |
| 4 | | | | | | |

6. በደረሰዉ የተሽከርካሪ አደጋ ጉዳት የደረሰበት ሴላ አካል ካለ ይገለጽ……………………………………
………………………………………………………………………………………………

7. በአደጋዉ የደረሰ የንብረት ጉዳት ……………………………………………………………

8. በፕላኑ መሰረት ተጠያቂ ተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር ……………የሾፌር ስም……………………

9. የመርማሪዉ/ትራፊክ ፖሊስ ስም………………………………ሞባይልቁጥር……………………

የፖሊስ ጣቢያው ማህተም

የአደጋዉ መለያ ቁጥር………………………ስልክ ቁጥር……………………ፊርማ……………………

ማስታወሻ : ይህ ቅጽ በ2 ኮፒ የሚታተም ሲሆን

- ዋናዉ ኮፒ ለመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት / ለሚመለከተዉ መድን ሰጪ ኩባንያ
- 2ኛዉ ኮፒ ለትራፊክ ፖሊስ ወይም ፖሊስ ይሆናል፡፡

መንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት ስልክ ቁጥር +251-118-55-38-44/+251-118-55-07-83
ነፃ አስቸኳይ የሕክምና አገልግሎት ለሁሉም የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጅዎች!!!

# የድንገተኛ /አስቸኳይ/ የህክምና አገልግሎት የክፍያ መጠየቂያ ቅጽ

ቀን ____________________

No. 5001

- ይህ ሪፓርት የሚሞላው በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት የድንገተኛ /አስቸኳይ/ ህክምና በሰጠ የህክምና ተቋም ነው፡፡
- ይህ ሪፓርት የሚሞላው የትራፊክ ፖሊስ ሪፖርት ለህክምና ተቋሙ ካቀረበ በኋላ ነው፡፡

1. የትራፊክ ፖሊስ የተሽከርካሪ አደጋ ሪፓርት
   ሀ. የአደጋ መለያ ቁጥር ____________________
   ለ. የአደጋው መርማሪው ትራፊክ ፓሊስ
      ስም ____________________
      መለያ ቁጥር ____________________
      ስልክ ቁጥር ____________________ የሞባይል ቁጥር ____________________
2. የታካሚው ዝርዝር መረጃ
   ሀ. ስም ____________________
   ለ. ዕድሜ ____________
   ሐ. ፆታ ☐ ወንድ ☐ ሴት
   መ. አድራሻ
   - ክልል/ከተማ ____________ ክ/ከተማ/ዞን ________ ወረዳ/ቀበሌ ________ የቤት ቁጥር ________
   - ስልክ ቁጥር ____________________ ሞባይል ____________________
   ሠ. የጉዳት ዓይነት ቀላል የአካል ጉዳት /ከባድ የአካል ጉዳት/ሞት/
3. ታካሚው የተሰጠው የህክምና ዓይነት
   ☐ በአደጋው ቦታ የተሰጠ የህክምና ዓይነት
   ☐ የድንገተኛ የአምቡላንስ /የትራንስፖርት አገልግሎት
   ☐ ህክምና ተቋም ድንገተኛ ክፍል የሚሰጥ የህክምና አገልግሎት
   ☐ በከፍተኛ ልዩ የህክምና እንክብካቤ ወይም ክትትል ክፍል
   ☐ የተሰጠው የህክምና አገልግሎት ከላይ ከተገለጹት ውጭ ከሆነ እባክዎት ይግለፁት

________________________________________

________________________________________

4. የህክምና አገልግሎት በህክምና ተቋማት ውስጥ
   ☐ ታካሚው በተመላላሽነት ታካሚ ነው፡፡
   ☐ ታካሚው በህክምና ተቋሙ ተኝቶ የሚታከም ነው፡፡
      ✓ ወደ ህክምና ተቋሙ የገባበት ቀን
      ✓ በህክምና ተቋሙ የወጣበት ቀን
5. የክፍያ ጥያቄ
   የክፍያ ጥያቄ የሚያቀርቡበት የህክምና አገልግሎት ዓይነትና የክፍያ መጠን ከዚህ በታች ይግለጹ፡-

| ተ.ቁ. | የህክምና አገልግሎት ዓይነት | የክፍያው መጠን | አባሪ ሰነዶች |
|---|---|---|---|
| 1. | | | |
| 2. | | | |
| 3. | | | |
| 4. | | | |

6. የህክምና ባለሙያውና የተቋሙ መረጃ፡-
   ሀ. ስም ____________________
   ለ. የሙያ ደረጃ ____________________
   ሐ. የህክምና ተቋሙ ስም ____________________
   መ. አድራሻ ____________________
   ሠ. ስልክ ቁጥር ____________________
   ረ. የፋክስ ቁጥር ____________________
   ሰ. የህክምና ተቋሙ ኃላፊ
      ስም ____________________
      ፊርማ ____________________
      የተቋሙ ማህተም

National Printing Press PLC